**የደብረጽዮን መድኃኔለም ቤ ክ የቦርድ አመራር አርብ ጥር ፳፯ ፳፻፲፫ ( Fri Feb 5 2021 ) ተሰብስቦ ከተወያየባቸውና ካሳለፋቸው አንዱ ቤተክርስቲያንን ላገልግሎት ለምእመናን ለመክፈት የመቼና እንዴት ውሳኔ ነበር።**

የኮቪድ 19 ወረርሺኝ ካመት በላይ በነበረው ቆይታ የሚያደርሳቸው የደዌ ከዚያም የከፋ የህይወትና የማህበራዊ ኑሮ ተካፍሎን ጨምሮ ሁላችንም የመድኃኔዓለም ቤተሰብ የምንረዳው ነው። ይሁን እንጂ ባምላክ ቸርነትና በሰውም የበኩሉን መወጣት ግዳጅ ካለፈው ወር ኢጋማሽ ጀምሮ ወረርሺኙና የሚያስከትለው ጥቃት ቀለል በማለቱ phase 4 የተባለ ከመዘጋጋት ለቀቅ ያለ ደረጃ ላይ ተደርሷል፡፡ በዚህ ደረጃ ደዌው እንዳይተላለፍ የሚደረጉ ጥንቃቄዎችን እንደተበራቱ በማቆየት፣ የተወሰኑ የህዝብ አገልግሎት ድርጅቶች የእምነት ድርጅቶችን ጨምሮ በጥንቃቄ ለተወሰነ የሰው ብዛት በራቸውን ሊከፍቱ በሚያስችል የስቴቱና የከተማዋ መሪዎችና የጤና አመራር ድርጅቶቻቸውም ተስማምተዋል ፡፡

የደብረጽዮን መድኅኔዓለም ቤክ ቦርድም ይህ ውጥን ውጤታማ በሚሆንበት መክሮ የሚከተሉትን ዝግጅቶች በማሟላት ቤተክርስቲያኗ ላሁኑ በቅድሚያ ለሚመዘገቡ 15 ምእመናን ከየካቲት ፲፬ ቀን 2ሺ13 (February 21, 2021) ዕለተሰንበት ጀምሮ በየሳምንቱ የሥርዓቱ አገልግሎት ተካፋይ እንዲሆኑ ወስኗል፡፡ ለምዝገባ chicagomedhanealem.org ገብተው የምዝገባ አቀናባሪዎችን ቁጥር በመደወል ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡

እቅዱ ውጤታማ እንዲሆን ሊደረጉ የሚገባቸው ቅድመ ዝግጅቶች

1 የምእመናን መገልገያ ቦታዎች፣ እቃዎች፣ መግቢያ መውጫዎች ተጸዳድተው መቋሚያዎችና የቅዳሴ መከታተያ መጻህፍት ተጠራርገው ይቆያሉ

2 የመግቢያ መውጫ በሮች እጀታና የሽንት ቤቶች ከ60% ያላነሰ አልኮል በሚይዙ ማጽጃ ፈሳሾች ይጸዳሉ

3 ማስከና የጅ መሸፈኛ በቅርቡ የተዘጋጁ መኖራቸው መሟላት ማስክም ከመግቢያው ጀምሮ በቆይታው ጊዜ ሁሉ እንዳጠለቁ የመቆየት ማሕበራዊ ግዴታዎች እንዲጠበቁ ይደረጋሉ፡፡

4 የጽዳትና የማስተናበር የማሳሰብና የማስተማር አገልግሎት በመስጠት የሚሳተፉ የቤተክርስቲያኒቱ ተጠሪዎችንም አማከሮ የሚጠበቀው የኮሮና ቫይረስ ለመተላለፍ ያለው እድል በሚቀጨበት ጥረቱም ተሟልቶ በሚቀጥልበት ቅድመ ዝግጅቶች መደርጋቸው የማያቋርጥ ነው፡፡

ግብረኃይሉ ቅድመ ዝግጅቱን በማጠናከር ባለበት ባሁኑ ጊዜ፣ቤተሰቡም ሥርአቱን ለመከታተል ወደቤተክርስቲያናችሁ በምትመጡበት ጊዜ እራሳቸውን መግታት ያልደረሱ ልጆችን ለማምጣት ከተገደዳችሁ የናንተው የቤተሰብ መቀመጫ ላይ በማስቀመጥና ጥበቃም በማድረግ እንዳይዟዟሩ ማድረጉ የምንጠብቀው ነው፡፡ የኮረናን ቫይረስ ላለማቅረብ ሁላችንም በምናደርገው ጥረት ሁሉ የመድኃኔዓለም ድጋፉ አይለየን።

**ከቺካጎ ደብረጽዮን መድኃኔዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤክ አስተዳደር።**